# በክስታኔ ማኅበረሰብ የለቅሶ ሥርዓት ክዋኔ የሲቢታ ሜራ ትዕምርታዊ እና ማኅበራዊ ፋይዳ ትንተና

በ

መሠረት ዓለሙ

ሰኔ፣2018 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# በክስታኔ ማኅበረሰብ የለቅሶ ሥርዓት የሲቢታ ሤራ ትዕምርታዊና ማኅበራዊ ፋይዳ ትንተና

በ መሠረት ዓለሙ

## አጠቃሎ[1]

ይህ ጥናት በክስታኔ ማኅበረሰብ የለቅሶ ሥርዓት ውስጥ የሲቢታ ሤራ ክዋኔ ትዕምርታዊ ትርጓሜና ማኅበራዊ ፋይዳ መመርመርን ዓላማው ያደረገ ሲሆን፤ በክስታኔ ማኅበረሰብ የለቅሶ ሥርዓት ውስጥ የሲቢታ ሤራ ሥርዓት እንዴት እንደሚከወን፣ በውስጡ የሚገኙት ትዕምርታዊ ድርጊቶች ምን ትርጉም እንዳላቸውና ይህ ሥርዓት ለማኅበረሰቡ የሚሰጠውን ማኅበራዊ፣ ሥነ ልቦናዊና ባህላዊ ፋይዳ ለመመርመር የተዘጋጀ ነው፡፡ጥናቱ ዓይነታዊ የጥናት ሥነ ዘዴን የተከተለ ሲሆን፣ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና ሰነድ ፍተሻ የተሰበሰቡት መረጃዎች በክዋኔ ተኮር ንድፈ ሐሳብ ማዕቀፍ ውስጥ ገላጭ ትንተና ዘዴን በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡የሲቢታ ሴራ በክስታኔ ማህበረሰብ የለቅሶ ሥርዓት ላይ ከሚፈፀሙ በርካታ ባህላዊ ክንዉኖች መካከል አንዱ ሲሆን በክስታኔ ማህበረሰብ የለቅሶ ሥነ-ሥርዓት ላይ ግብዓተ መሬት ከተፈፀመ በኋላ ከሚከናወኑ ሥርዓቶች የመጀመሪያዉና ጉልህ ስፍራ የሚሰጠዉ ስርዓት ነዉ፡፡ በሥርዓቱም ሟችና ቤተሰቦቹ የነበራቸው መረዳዳት በይፋ የሚመሰከርበት ቤተሰባዊና ማህበራዊ ግዴታቸዉን የተወጡ የሚመረቁበት፣ ቤተሰባዊና ማህበራዊ ግዴታቸውን ያልተወጡ ደግሞ የሚረገሙበት መድረክ ነው፡፡ በመሆኑም ሰዎች በሕይወት እያሉ መልካም እንዲሰሩና ቤተሰቦቻቸዉን እንዲረዱ ስነ-ልቦናዊ ተፅዕኖ በማሳደር የሟችንና የቤተሰቡን መልካም ስም በማስጠበቅ፣ ማኅበራዊ ትስስርን በማጠናከርና ባህላዊ እሴቶችን በማስቀጠል ረገድ የላቀ ሚና ያለዉ ነዉ፡፡ ይህ ክዋኔ ማኅበረሰቡ ስለ እውነት፣ ስለ ፍትሕና ስለ ቤተሰባዊና ማኅበራዊ ግዴታዎች ያለውን አመለካከት የሚያንፀባርቅበት ነው፡፡ በተጨማሪም ሥርዓቱ የሟች ልጆች ለወላጆቻቸው፤ ወላጆችም ለልጆቻቸዉ ያደረጉትን እንክብካቤና ሀላፊነት የመወጣት ሚና የሚመዘንበትና ማኅበራዊ ተቀባይነት የሚያረጋግጥበት መድረክ ነው፡፡

[1] ይህ መጣጥፍ በክስታኔ የለቅሶ ሥነስርዓት ክዋኔ በሚል ርዕስ የ2018 ዓ.ም. ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፌ ባቀረብኩት ጥናታዊ ጽሁፍ ተወስዶ ለአውዱ እንዲስማማ ሆኖ የቀረበ ነው

## 1. መግቢያ

የሰው ልጅ በሕይወት ዘመኑ ከሚያጋጥሙት ተፈጥሯዊ ክስተቶች ውስጥ አንዱ ሞት ነው። ሞት የሰውን ልጅ ከሚወደውና ከለመደው ዓለም፣ እንዲሁም ከቤተሰቡና ከወዳጅ ዘመዶቹ የሚነጥል ክስተት በመሆኑ የሐዘን ስሜትን ይፈጥራል። ይህን የሐዘን ስሜት ለመግለጽና ሟቹን ለመሸኘት የተለያዩ ማኅበረሰቦች የየራሳቸው የሆነ የለቅሶና የቀብር ሥነ ሥርዓት አላቸው። በሀገራችን ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችም እንደየባህላቸው፣ እምነታቸውና የሕይወት ፍልስፍናቸው የተለያየ የለቅሶ ሥርዓት ይከውናሉ።

ከእነዚህ ብሔረሰቦች መካከል አንዱ የሆነው የክስታኔ ማኅበረሰብም የራሱ የሆነ የዳበረና ትዕምርታዊ ይዘት ያለው የለቅሶ ሥርዓት አለው። የማኅበረሰቡ የለቅሶ ሥርዓት ድንገት ተከስቶ የሚያልፍ ክንውን ሳይሆን፣ ማኅበረሰቡ ስለ ሕይወት፣ ስለ ሞት፣ ስለ ቤተሰባዊና ማኅበራዊ ትስስር፤ ስለ እሴቶቹ ያለውን ጥልቅ የዓለም አተያይ የሚያንፀባርቅበት መድረክ ነው። በማኅበረሰቡ የለቅሶ ሥርዓት ውስጥ ከሚከናወኑት በርካታ ክዋኔዎች መካከል ልዩ ትኩረት የሚስበውና ማኅበራዊ ፋይዳ ያለው ሥርዓትም ነው።

### 1.1 የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናት በክስታኔ ማኅበረሰብ የለቅሶ ሥርዓት የሲቢታ ሜራን ክዋኔ መግለፅ፤ ትዕምርቶችን መፈከርና ማህበራዊና ስነ-ልቦናዊ ፋይዳ መተንተንን ነዉ።

### 1.2 የጥናቱ ጥያቄዎች

ይህ ጥናት ሁለት መሠረታዊ ጥያቄዎችን ይመልሳል፦

1. በክስታኔ ማኅበረሰብ የለቅሶ ሥርዓት የሲቢታ ሜራ ዓውዳዊ ክዋኔ ምን ይመስላል?
2. በሲቢታ ሜራ ክዋኔ ወቅት የሚታዩ ትዕምርቶች ማኅበራዊና ስነ-ልቦናዊ ትርጓሜያቸው ምንድን ነው?

### 1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ

1. የክስታኔ ማኅበረሰብ የለቅሶ ሥርዓት የሲቢታ ሜራን ክዋኔ በዓውዳዊ ጥናት በተደገፈ መረጃ በጽሑፍ ሰንዶ በማቆየት ታሪካዊና ባህላዊ ሚና ይኖረዋል።

2. በማኅበረሰቡ የለቅሶ ክዋኔ ላይ ያሉ ልምዶችን፣ የእርስ በርስ መረዳዳት እሴቶችንና የማኅበራዊ ፍትሕ አሰጣጥ ሒደቶችን በማሳየት ባህሉን ለቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ ያግዛል::
3. አንድ ማኅበረሰብ በሚያከናውነው የለቅሶ ሥርዓት አማካይነት ስለ ሕይወት፣ ስለ ሞት፣ ስለ ማኅበራዊ ግዴታዎችና ሥነ ምግባር ያለውን አመለካከት የሚያሳይ በመሆኑ፣ የክስታኔ ማኅበረሰብን የዓለም አተያይ ለመረዳት ለሚፈልጉ ሰዎች፣ተመራማሪዎች እንዲሁም የትውፊታዊ ጥበብ ባለሙያዎች እንደ መነሻ ሐሳብ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል::

### 1.4. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው ከክስታኔ ማኅበረሰብ የለቅሶ ሥርዓት መካከል የሲቢታ ሤራን ማጥናትና መተንተን ላይ ነው:: የክስታኔ ማኅበረሰብ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኝ ቢሆንም፣ የጥናቱ መልክዓ ምድራዊ ወሰን በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት፣ በምሥራቅ ጉራጌ ዞን፣ ደቡብ ሶዶ ወረዳ  ላይ ብቻ የተወሰነ ነው::

### 1.5. አካባቢያዊ ና ማህበረ-ባህላዊ ዳራ

የክስታኔ ማኅበረሰብ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት፣ በምሥራቅ ጉራጌ ዞን  የሚገኝ ሲሆን አብዛኛው የማኅበረሰቡ አባል በደቡብ ሶዶና ሰሜን ሶዶ ወረዳዎች ውስጥ የሚኖር ነዉ:: መተዳደሪያውም በዋናነት ግብርናና ንግድ ነው::  ማህበረሰቡ   ክስታኔ፣ አይመለል፣ ኅርደናና ሶዶ  ጉራጌ በሚሉ የተለያዩ ስያሜዎች  የሚታወቅ  ሲሆን በዋናነት 'ክስታኔ' በመባል ይጠራል::

የክስታኔ ማኅበረሰብ በሕብረትና በመረዳዳት የሚኖርና ሥራ ወዳድ ነው:: በማኅበረሰቡ ዘንድ ሥራ የማይሰራ ሰው ይናቃል፤ ይወገዛል፤ ይጠላል:: በመሆኑም በቤተሰብ ውስጥ ከልጅነታቸዉ ጀምሮ የሥራ ክፍፍል ማድረግ የተለመደ ነው:: የክስታኔ  ልጆች አድገው ራሳቸውን ሲችሉም ሥራ ሰርተዉ ለቤተሰብ  ማድረግ ይጠበቅባቸዋል:: አንድ ልጅ የራሱን ኑሮ መኖር ከጀመረ የግድ ቤተሰቦቹን መርዳት ይኖርበታል:: በቤተሰቡ አቅራቢያ የሚኖር ከሆነ ሲታመሙ ማስታመም፣  በሥራ ሲደከሙ ማገዝና መርዳት ይኖርበታል:: ከቤተሰቦቹ ርቆ የሚኖር ከሆነም ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ለመስቀል በዓል ትውልድ ሀገሩ መግባትና ለወላጆቹ  አስፈላጊ ነገሮችን ማድረግ ይጠበቅበታል:: ይህን ካላደረገ ግን በቤተሰቦቹ ከዚያም አልፎ በጎረቤቶቹ መጥፎ ሥራው ሲወሳ ይኖራል:: በሀገር ሽማግሌዎችም ይረገማል::

የክስታኔ ማህበረሰብ በምርቃት ላይ ያላቸዉ እምነት ከፍተኛ ነዉ። በሀገር የልማት፣ የአስተዳደር፣ በእርቅ ጉዳይ ፣ በሰርግና በማንኛዉም የግብዣ ሥነ-ሥርዓት ላይ ሲገናኙ ሽማግሌዎች ሀገር ሰላም እንዲሆን፣ የሀገር መሪዎች ከክፉ እንዲጠበቁ ለመንደሩ ለምድሪቱ ፣ ለአዛዉንቱና ለወጣቱ በተሰማራበት የሥራ መስክ ስኬታማ እንዲሆን ይመርቃሉ።

የክስታኔ ልጆችም በወላጆቻቸዉ ምርቃት ትልቅ በረከት እንደሚጎናፀፉ እና በተሰማሩበት በማንኛዉም የሕይወት ጎዳናዎች ስኬት እንደሚያገኙ ስለሚያዉቁ ከየትኛዉም የሀገሪቱ ክፍል ወላጆቻቸዉን ለመጠየቅ ወደ ትዉልድ ሀገራቸዉ ይሄዳሉ። በተለይ በመስቀል በዓልና በፆም እኩል (ደብረ ዘይት) ልጆች የቦታና የሀገር ርቀት ሳያግዳቸዉ ብዙ ኪሎሜትሮችን አቋርጠዉ በመምጣት ወላጆቻቸዉ ዘመዶቻቸዉና ጎረቤቶቻቸዉ የሚያስፈልጋቸዉን በሚሟላት ምርቃት ይቀበላሉ። የምርቃት ሥርዓቱም ሦስት ወይም አምስት ሽማግሌዎች ሲመርቁ ሌላዉ ህዝብ አሜን በማለት ምርቃቱን ይቀበላል ሽማግሌዎቹም በየተራ መርቀዉ ሲጨርሱ "ኬር ዬሁን" በማለት ህብር ባለዉ ዜማዊ ድምፅ ያፀድቃሉ። የክስታኔ ልጆች በምርቃት ውስጥ በረከት እንዳለ ስለሚያምኑ፣ መልካም ተግባርን በማድረግ መመረቅን እንጂ በማንም ቢሆን መረገምን አይፈልጉም።ምርቃትም ሆነ እርግማን በኑሮአቸዉ እና በዘራቸዉ ላይ የሚያመጣዉ ዉጤት እንዳለ በፅኑ ያምናሉ። (ፍቃዱ:2013)ይህ የምርቃት ሥነሥርዓት በማህበሠሰቡ የለቅሶ ክዋኔ የሲቢታ ሴራ ስርዓት ላይ በጉልህ ይታያል።

የክስታኔ ማህበረሰብ የራሱ የሆነ ባህላዊ መተዳደሪያ ህግ አለዉ። ይህ ባህላዊ ሕግ የጎርደና ሴራ(ህግ) ተብሎ ይጠራል። ይህ ባህላዊ ህግ የማህበረሰቡን የመሬት የአስተዳደር ሥርዓት፣ የጋብቻ ሥርዓት፣ የአባትና እናት የመጦር ሥርዓት፣ የእርቅሥርዓት የለቅሶ ሥርዓት ወዘተ የያዘ ነዉ። የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነዉ የሲቢታ ሤራ( ህግ) ም ከዚሁ የጎርደና ሤራ ዉስጥ የሚገኝ ባህላዊ ህግ ነዉ።

### 1.6. የጥናቱ ሥነ ዘዴ

ለዚህ ጥናት ተግባራዊ የሆነው የምርምር ዘዴ ገላጭ (Descriptive Study) ነው። ገላጭ የምርምር ዘዴ ነባራዊ ሁነቶች ያላቸውን ተፈጥሯዊ ባህርይ በመለየትና በዝርዝር በመተንተን ለመግለጽ የሚያስችል ዘዴ ነው (Koul, 2006)። እንደ ምሁሩ ገለጻ፣ ዓይነታዊ ገላጭ ጥናት በግልጽ የማይታዩ የሰው ልጅ ስሜቶች፣ ልማዳዊ እምነቶችና ዕውቀቶች ያላቸውን ማኅበራዊና ባህላዊ ትርጉም ለመረዳት ይረዳል።

ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለማግኘት  መሠረታዊ ዘዴዎች ማለትም ምልከታና ቃለ መጠይቅ ሥራ ላይ ውለዋል። ምልከታ በሚጠናው ማኅበረሰብ ውስጥ በአካል በመገኘት፣ የሚከወኑ ድርጊቶችን በማየትና የሚነገሩ ቃላትን በመስማት መረጃ የሚሰበስብበት ዘዴ ነው። ለዚህ ጥናት   በደቡብ ሰዶ ወረዳ ኑረና ቀበሌ በመገኘት  የሲቢታ ሄራ ሥርዓት ክዋኔዎችን፣ ትዕምርታዊ ተግባራትንና ተሳታፊዎች የሚያሳዩትን ስሜት ለመረዳት ምልከታ ተደርጓል። መረጃዎቹም የተሰበሰቡት ክዋኔው በሚከናወንበት ተፈጥሯዊ መቼት ውስጥ ነው

## 2. የሲቢታ ሄራ ክዋኔ

የሲቢታ ሄራ በክስታኔ ማህበረሰብ የለቅሶ ሥርዓት ላይ ከሚፈፀሙ በርካታ ባህላዊ ክንዉኖች መካከል አንዱ ሲሆን በክስታኔ ማህበረሰብ የለቅሶ ሥነ-ሥርዓት ላይ  ግብዓተ መሬት ከተፈፀመ  በኋላ ከሚከናወኑ ሥርዓቶች የመጀመሪያዉና ጉልህ ስፍራ የሚሰጠዉ ስርዓት ነዉ።  ይህ ሥነ ሥርዓት ለቀስተኛዉ ቀብሮ እንደተመለሰ ቤተ ክርስቲያን ግቢ ዉስጥ ወይም ቤተክርስቲያን አቅራቢያ ባለ ሰፊ ስፍራ በመሰብሰብ የሚከወን ነዉ ። ሥርዓቱም በሟችና በቤተሰቡ መካከል ያለውን ማህበራዊ ግዴታ የሚፈትሽበት  ሂደት ነው:::: የሲቢታ  ሴራ የማህበረሰቡ   ባህላዊ መተዳደሪያ ከሆነዉ የጎርደና ሴራ(ደንብ)  የወጣ ሴራ (ደንብ)ሲሆን በሟችና በቤተሰቡ መካከል የነበረዉን ቤተሰባዊ ግንኙነት በመገምገም ልክ ለሆነዉ ተግባር የሚያሞግስ(የሚመርቅ) ስህተት የነበረዉን የሚወቅስ(የሚረግም)ና  እዉቅና የሚሰጥ ሥርዓት ነዉ።

### 2.1. የሲቢታ ሄራ ሥርዓት መዋቅርና የሽማግሌዎች ሚና

በክስታኔ ማህበረሰብ የለቅሶ ሥርዓት ክዋኔ የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ ተፈጽሞ ሕዝቡ ከቤተክርስቲያን ሳይበተን፣ የሲቢታ ወገን የሆነ ሰው ከቁመቱ  በላይ የሆነ ረዥም ቀጭን ዘንግ ይዞ በሀዘንተኞችና ለቀብር ተሰብስቦ በቆመዉ ሰው

ፊት በአንድ እግሩ   ተንበርክኮ እንዲህ በማለት ሥርዓቱን ይጀምራል የሲቢታ ሄራ ሄራ የሁንክም፣ የእንጀሪ ሄራ ሄራ የሁንክም የአምስቱ አለንጋ ሄራ ሄራ የሁንክም፤በማለት ይህንን ባህላዊ ህግ የደነገጉትን አምስቱ  የቤተ ጉራጌ ተወካዮች(አምስት አለንጋ) በማለት፤ የተደነገገበትን ቦታ(እንጀሪ) በመጥቀስ አሁን እኛ ይህንኔ ሄራ(ህግ) የምንሰጣችሁ ዛሬ ባመጣነዉ ደንብ ሳይሆን ቀደምት አባቶቻችን በተስማሙበት እኛም ተስማምተን በምንመራበት ህግ ነዉ በማለት አፅንኦት በመስጠት ሥርዓቱን ይጀምራል። ደንብ ሰሪዉ(የሥርዓቱ አስፈፃሚ) የሟች ልጆች፣

የቅርብ ዘመዶች፣ ሚስት ወይም ባል እናት አባት ሟቹን በሕይወት ሳለ እንዴት ይንከባከቡት እንደነበር ጥያቄ ያቀርባል። "ሰቦች አዉድሙ" ሰዎች ተናገሩ በማለት ቤተሰቦቹ ሟቹን ሲረዱት፣ ሲንከባከቡትና፣ሲደግፉትና ሲጦሩት ነበርን? በማለት ጐረቤቶችንና የቅርብ ሰዎችን በምስክርነት ይጠይቃል። ይህ ሂደት በማህበረሰቡ ዘንድ የልጅ፣ የወላጅና የዘመድ የመንከባከብ ኃላፊነት በተግባር የሚመዘንበት መድረክ ነው።

ምስክርነት የሚሰጡት ሦስት ጎረቤቶች ወይም የቅርብ ሰዎች በራሳቸዉ ፈቃድ፣ ስለ ሟቹ እና ስለ ሟች ቤተሰብ ጥሩም ሆነ መጥፎ ስራ በየተራ ምስክርነት ይሰጣሉ። ሟች ለቤተሰቡ ለአካባቢዉና ለሀገሩ ስላበረከተዉ አስተዋፆም ሆነ አሉታዊ ነገር፤ የሟች ቤተሰብም ሟቹን በህይወት እያለ ስለመንከባከባቸዉና መርዳታቸዉየሚያዉቁትንይመሰክራሉ።ሲጨርሱ ሄራውን የሚሰጠዉ ሰው(የሥርዓቱ አስፈፃሚ) የደሬ በል ይላል መስካሪዉም "የደሬ" ይላል።"የደሬ" ማለት የመሰከርኩት የዉሸት ቃል ካለዉ ግፍ በእኔና በቤተሰቤ ይድረስ እንደማለት ነዉ። ። (ምልከታ 28/04/2018 ኑሪና)

### 2.2. በሲቢታ ሄራ ስርዓት መልካም ለፈጸሙ ቤተሰቦች

ሟቹን የተንከባከቡ የረዱ፣ ያስታመሙና እስከመጨረሻው አጠገቡ የነበሩ መሆናቸው በምስክርነት ከተረጋገጠ፣ ደንብ ሰሪዉ (የህግ አስፈፃሚዉ) ቤተሰቡን ስለ መልካም ስራቸዉ በሕዝብ ፊት ይመርቃቸዋል። ይህ ምርቃት "መልካም ተግባር ሰርታችኋልና ሐዘን አይግባችሁ" እንደማለት ነዉ። በዚህ ጊዜ ሐዘንተኞቹ ከሕዝቡ መካከል ተለይተው እንዲቀመጡ ይደረጋል። ይህም ለፈጸሙት መልካም ተግባር የሚሰጥ ትልቅ ማህበራዊ እውቅናና በረከት ነው።

ይህንን አስመልክቶ መረጃ ሰጪዎች እንዲህ በማለት ይገልፃሉ፦ ሟች በህይወት እያለ ከተንከባከበ ከጠየቀ ከጦረና ካስታመመ ከጎረቤት የሚደበቅ ስላልሆነ የሚያዉቁትን ተናግረው 'የደሬ' ብለው ይምላሉ ይህም ውሸት ተናግረን ከሆነ ግፍ በኛና በልጆቻችን ይድረስ ማለት ነዉ።ይህም እንዳይዋሹ እና እውነታውን እንዲናገሩ ለማድረግ የሚፈጸም ነው። በመሆኑም ከዋሹ በርቺ (ግፍ) ይሆንብናል፤ መከራ ይደርስብናል ተብሎ ስለሚታመን የውሸት ምስክርነት ለመስጠት አይደፍሩም። ደንብ ሰሪዉም ቃላቸዉን ከሰማ በኋላ ብልጫ ተመራቂ አለ ?ብሎ ይጠይቃል ካለ ያሳዉቃሉ ወይም ደግሞ ሽማግሌዎች እራሳቸዉ ሟች በህይወት እያለ ቤተሰቡን በሙሉ ወይም እከሌን ብልጫ መርቁልኝ ብሎ ቀድሞ ተናዟል በማለት ያሳዉቃሉ። በዚህ

መሰረት በሥርዓቱ መጨረሻ በኑዛዜዉ መሰረት ቅቤ የሚቀባዉ ቅቤ ተቀብቶ ነጭ ሻሽ ታስሮላቸዉ ይመረቃሉ።(ቃ.መ.፣28/04/2018)

## 2.3. የሲቢታ ሤራ ሥርዓት አፈጻጸም ለአጥፊዎች

ሟቹ በሕይወት እያለ ያልረዱ፣ ያላገዙ ፣ ያልጠሩ ወይም በህመሙ ወቅት አጠገቡ ያልነበሩ መጥተዉ ያልጠየቁትን የቤተሰብ አባላትና ዘመዶች ካሉ በማህበረሰቡ ሕግ መሠረት ጎረቤት በሆኑ ወይም ቤተሰቡን በቅርበት በሚያውቁ ሦስት ምስክሮች ተለይተው እንዲታወቁ ይደረጋል። እነዚህ አጥፍተዋል ቤተሰቡ በሚፈልገዉና በሚያስፈልገዉ ነገር አልረዱትም የተባሉት ግለሰቦች ከሕዝቡ መካከል ወጥተው እንዲቆሙ ወይም እንዲለዩ ይደረጋል። በሥርዓቱ መሠረት ጥፋተኛ ተብለው ስለሚታሰቡ፣ በማህበረሰቡ ፊት እንዲገለሉ በማድረግ ማህበራዊ ቅጣት ይጣልባቸዋል። ይህም ግለሰቡ በማህበረሰቡ ዘንድ ያለውን ተቀባይነት የሚያሳጣና ትልቅ ውርደት ተደርጎ የሚወሰድ ነው። ይህንን አስመልክቶ መረጃሰጪዎች እንዲህ ያብራሩታል፦

ሟች በህይወት እያለ የሚገባዉን ካላደረገ ካላገለገለ፣ ካልጠረና ካላስታመመ በለቅሶ ላይ ይህ ይነገርበታል ሟች ተቸግሮ ነዉ የሞተዉ፤ ታሞ አላስታመመዉም፤ አልጠየቀዉም፤ የሚገባዉን አላደረገለትም፤ ተብሎ ይመሰከርበታል ይህን ጊዜ በል ከዚህ ዉጣ ተብሎ ልብሱን ተገፎ(ራቁቱን) ፊቱን አዙሮ እንዲሄድ ይደረጋል(ቃ.መ፣28/04/2018)

በመጨረሻም "ዚ ብሽ ላይመጣየን የለ ለላለ ይመጣው ለታተ ይመጣው ደመኘን ፣ አኢደኘን ፣ ዋስተኘን ፣ አይበሉ ኪት አርባ ድረስ የብሽም የግባ የብሽም የውጣ ዚ ሤራ ያምስት አለንጋ ሤራ ፣ የእንጀረ ሤራ፣የሲቢታ ሤራ ፣ የጎይታ ሤራ የሁንክም ፣ ዚ አውድሙም ትረፍም የብሽ ሴራ አብነም።"በማለት ከተለያዩ አካባቢዎች ለቅሶ ለመድረስ ቤተሰቡን ለማፅናናት የመጡና የሚመጡ ሰዎች እንዳሉና ደመኛዬ ነዉ፣ ገንዘብ ተበድሮኝ ነበር፣ ዋስሆኖ ተሰዉሮ ነበር፣ በማለት ምንም ዓይነት ችግር እንዳያደርሱባቸው እስከ ሰማንያ ቀን ድረስ ለቅሶ ሊደርስ ሲመጣ እንዳይነካ በማለት ለለቅሶ ደራሹ የጥበቃ ሕግ (ሴራ) ይታወጃል። በመቀጠልም ለሀዘንተኞች በአባቶቻችን ህግ መሰረት ለቅሶ ሰጥተናችኋል ለቅሶ መቀመጥ ትችላላችሁ ሰዉም ያፅናናችሁ በማለት የማረጋገጫ ቃል ይሰጣቸዋል:::: ይህም ለለቅሶ ደራሹ በለቅሶ ላይ እንዳለ እንዳይያዝ ያበደረውን መልስ ተብሎ እንዳይከሰስ የሚገዝትና የእንግዶችን(የለቅሶ ደራሹን) ደህንነት በማረጋገጥ ማህበራዊ ግዴታዉን እንዲወጡ የሚያደርግ ሲሆን ፤ ለሐዘንተኛው ደግሞ ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት

መጥተዉ እንዲያፅናኑት  በማድረግ ስነ-ልቦናዊና ማህበራዊ መረጋጋት እንዲሰፍን የሚያደርግ የማህበረሰብ ሕግ ነው።

ከዚህ በኋላ ቤተሰብንና አካባቢን መርቆ ሀገር ሰላም እንዲሆን ተመኝቶ በማህበረሰቡ እኩይ የሚባሉትን ምግባራት ሌብነት፣ ምቀኝነትና አድመኝነትን አዉግዞ የከዋኔዉ ፍፃሜ ይሆናል። (ምልከታ፣28/04/2018)

ይህ የሲቢታ ሜራ ሥርዓት  ግለሰቦች ለቤተሰቦቻቸውና ለማህበረሰባቸው ያላቸውን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጡ የሚያስገድድ፣ ታማኞችን የሚያከብርና ኃላፊነታቸውን ያልተወጡትን ደግሞ በሕዝብ ፊት የሚቀጣ ለአካባቢና ለማህበረሰብ ሰላም የሚያሰፍን ጠንካራ የማህበራዊ ስነምግባር  መቆጣጠሪያ ዘዴ ነው።

### 2.4. የሲቢታ ሜራ ትዕምርታዊ ማኅበራዊና ስነ-ልቦናዊ ፋይዳ ትንተና

በክስታኔ ማኅበረሰብ የለቅሶ ሥነ ሥርዓት  የሲቢታ ሜራ ክዋኔ ማኅበረሰቡ ለፍትሕ፣ ለእውነትና ወላጅን ላለመርሳት ለሰጠው የሞራል ልዕልና ሕያው ማሳያ ነው።

ሜራውን  የሚሰጠዉ ሰው(ህግ አስፈፃሚዉ) ወይም ሥርዓቱን የሚመራው በአካባቢው ቀደምት ሰፋሪዎች ከሆኑት ከሲቢታ ወገን የተገኘ ሰው ነው። የዚህ ሥርዓት አፈጻጸም ማራኪና ትዕምርታዊ ይዘት ያለው ነው። ሥርዓቱን የሚያስፈጽመው ሰው ከቁመቱ የሚበልጥ ቀጭን ዘንግ ተመርኩዞና በአንድ እግሩ ተንበርክኮ ሥርዓቱን ይፈፅማል።  የሜራው አስፈጻሚ በአንድ እግሩ ቆሞ የማኅበረሰቡ መሰረት የሆነውን ሥርዓት መፈጸሙን ከማኅበረሰቡ ሃይማኖት ጋር አያይዘው ይገልፁታል። ለዚህም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት በአንድ እግራቸው ለሰባት ዓመታት በመጸለያቸው የሚታወቁት ኢትዮጵያዊው ጻድቅ አብነ ተክለ ሃይማኖት በአካባቢው መስበካቸውንና ማስተማራቸውን በማስታወስ ከዛ የመጣ ሊሆን እንደሚችል ያስረዳሉ። በአንድ እግር መቆም ከባድና የሰውነት ሚዛንን የሚያስት ሲሆን፣ ሜራውን የሚያስፈጽመው ሰው ሥርዓቱን እስኪጨርስ ለአስርና አስራ አምስት ደቂቃ በአንድ እግሩ መቆም የሚችለው በሚመረኮዘው ዘንግ ድጋፍ ነው። ስለዚህ የሜራ አስፈጻሚው በአንድ እግሩ መቆም ከሚመረኮዘው ዘንግ (በትር) ጋር ተያይዞ የሚታይ ነው። በትሩ የሥርዓት፣ የሥልጣንና የኃይል ትዕምርት ነው። ሜራ ፈጻሚው ሚዛኑን ሳይስት መቆም ያስቻለው የሥርዓቱ ትዕምርት የሆነውን በተር በመመርኮዙ እንደሆነው ሁሉ ማኅበረሰቡም ይህን ሥርዓት በመከተል ማኅበራዊ ህልውናው ሳይናጋ መቆየት እንደሚችል አመላካች ነው።

ከለቀስተኛው መሀል ሦስት የሟች ጎረቤቶች ወደ ፊት እንዲወጡ በማድረግ፣ ስለ ሟችና ስለ ሟች ልጆች እውነተኛ ምስክርነት እንዲሰጡ ይጠየቃሉ፡፡ ምስክሮቹ እውነት ካልተናገሩ በርቺ ወይም መቅሰፍትና ግፍ ይደርስብናል ብለው ስለሚያምኑ የሚያውቁትን እውነት ብቻ ያለ ምንም መሸፋፈን ለአደባባይ ያቀርባሉ፡፡ ሥርዓቱ "ዛሬ በሟች ላይ የምትሰጠው ምስክርነት ነገ በአንተ ላይ ይሰጣል" የሚል ስነ-ልቦናዊና ትዕምርታዊ ማስጠንቀቂያ ያስተላልፋል፡፡ ምስክሮቹ የሚጠየቁት ጥያቄዎች የማኅበረሰቡን የሞራል መሠረት የሚፈትሹም ናቸው፡፡ በመስካሪዎች ቃል መሰረትም ቤተሰቡ ይመረቃል ወይም ይረገማል፡፡

ምርቃትና ርግማን በሲቢታ ሴራ ውስጥ እንደ ተራ ንግግር ሳይሆኑ፣ እንደ ማህበራዊ ፍርድ እና የሞራል ሚዛን ትዕምርቶች ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ጎረቤት መጥቶ የሚሰጠው የምስክርነት ቃል የግለሰቡን ማህበራዊ ማንነት የመቅረጽ ኃይል አለው አባትን ወይም እናትን በአግባቡ መጦር በማኅበረሰቡ ዘንድ ለቀብር ማስፈጸምና ለቅሶ ለመቀመጥ እንደ ቅድመ ሁኔታ መታየቱ ልጆች ወላጆቻቸውን የማክበር ባህል ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲሸጋገር የሚያደርግ ጠንካራ ማኅበራዊ ተቋም ነው፡፡እያንዳንዱ ተሳታፊ በሲቢታ ሴራ ወቅት የሟቹን ግምገማ ሲሰማ፣ የራሱን የነገ ማንነት በመስታወት እንደማየት ይቆጥረዋል፡፡ መልካም ተግባር የፈፀመ ቤተሰብ ሲመረቅ "ዘሩ ይባረክ፣ ቤቱ ይቅና" ይባላል፤ ይህም በጎነት ተባዝቶ ለትውልድ እንደሚተርፍ ያመለክታል፡፡ ምርቃት የልምላሜ የሰላምና የማህበራዊ ተቀባይነት ትዕምርት ነዉ፡፡

በተቃራኒው፣ ምስክሮቹ ልጆቹ ወላጃቸውን እንዳልጦሩ፣ እንዳላገለገሉና ወላጁ ተቸግሮ እንደሞተ ከመሰከሩ፣ ወላጅም ለልጁ የሚገባዉን ሳያደርግ ከሞተ በሕዝብ ፊት ይዋረዳሉ፡፡ የልጅነትና የወላጅነት ኃላፊነታቸውን አልተወጡም ተብሎ ስለሚታመን፣ ራቁታቸውን እንዲሄዱ ይደረጋል፡፡ ውጣ! ለቅሶ አይሰጥም! ተብሎ ስለሚባረሩ ለቅሶ መቀመጥ አይፈቀድላቸውም፡፡ ማንም ሰው አያጽናናቸውም፤ ከማኅበራዊ መስተጋብርም ይገለላሉ፡፡

ርግማን፦ከማህበረሰቡ የመገለል እና የውድቀት ትዕምርት ነው፡፡ ማህበራዊ ግዴታውን ያልተወጣ ሰው ሲረገም ድርጊቱ ለሌላው ትውልድ እንደ ማስጠንቀቂያ ያገለግላል፡፡ ይህ የሲቢታ ሤራ ፍርድ፣ ሕይወት ላለው ሰው ሁሉ ትልቅ የማንቂያ ደወል ነው፡፡

በሥርዓቱ ወቅት የሚሰጡት ምርቃትና ርግማን በማህበረሰቡ ውስጥ ትልቅ የሞራል ግፊት ይፈጥራሉ መልካም የሆኑና የረዱ የሚመረቁበት፣ ማህበራዊ ግዴታቸውን ያልተወጡና ያልረዱ

(ያላገለሉ) ደግሞ የሚረገሙበት መሆኑ፣ ሰዎች በሕይወት ሳሉ ከነውር እንዲርቁና ለቤተሰቦቻቸዉ ደራሽ እንዲሆኑ በማድረግ እንደ ሥነ-ምግባር መቆጣጠሪያነት ያገለግላል።

የሲቢታ ሴራ ማህበራዊ ጠቀሜታዉን ስንመለከት በሟች ቤተሰቦች እና በማህበረሰቡ መካከል ያለውን ግንኙነት መልሶ የሚያጸናበት ፤ጎረቤቶች መጥተው ስለ ሟች ቤተሰብ መልካምነት ሲመሰክሩ ቤተሰቡ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ክብርና ቦታ እንዲጠናከር በማድረግ ማህበራዊ ትስስር እንዲጠናከር የሚያደርግበት፤ ባህላዊ እሴቶችና ሀገር በቀል ዕውቀት የሚሸጋገርበትና ለስነምግባር መቆጣጠሪያነት የሚገለገልበት ባህላዊ ህግ ነዉ።

የሲቢታ ሄራን ከስነ ልቦናዊ ማዕቀፍ አኳያ ስንመረምረው መልካም ምስክርነት ያገኙ ቤተሰቦች ማህበረሰቡ ከጎናቸው መሆኑን በተግባር ስለሚያዩ፣ በሐዘን ወቅት የሚሰማቸውን የብቸኝነትና የባዶነት ስሜት በመቀነስ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ ስለሚኖረው ስነ-ልቦናዊ ዋስትና እና መረጋጋትን ይሰጣል። በሕይወት ሳለ የፈጸማቸው በጎ ተግባራት በይፋ መመዝገባቸው ለቤተሰቦቹ ትልቅ ስነ-ልቦናዊ እረፍት ይሰጣል።

ሥርዓቱ የግለሰቡንና የቡድኑን ሥነ ልቦናዊ ሚዛን የመጠበቅ ዓላማ አለው። የሟች ልጆች በሕይወት ዘመናቸው አባታቸውን ወይም እናታቸውን በአግባቡ መንከባከባቸው ወላጆችም ለልጆቻቸዉ የሚገባቸዉን ማድረግ ማኅበረሰቡ የሚጠብቅባቸው ማኅበራዊ ሚና ነው። ሆኖም ይህን ኃላፊነት ሳይወጡ ቀርተው በራስ ወዳድነት ከተመሩ፣ የሲቢታ ሄራ ይህንን ማንነታቸውን አደባባይ በማውጣት ማኅበራዊ ፍርድ ይሰጣል። ይህ ምግባር ከማኅበረሰቡ መለኪያ ጋር የማይስማማ፣ ያልሰለጠነ ማንነት በመሆኑ፣ ደንብ ሰሪዉ( ህግ አስፈፃሚዉ) እና ምስክሮቹ ይህንን ማንነት አጋልጠው ግለሰቡን ከማኅበረሰቡ ይነጥሉታል። ሥርዓቱ የጋራ እሴቶችን ከራስ ወዳድነት በላይ አድርጎ በማስቀመጥ የቡድኑን ህልውና ይጠብቃል።

ይህ የፍትሕና የማኅበራዊ ዕውቅና ሥርዓት ሲጠናቀቅ ደንብ ሰሪዉ(የሥርዓቱ አስፈፃሚ) እንደአጀማመሩ ሁሉ ሄራውን የደነገጉትንና ሄራዉ የተደነገገበትን ቦታ አንስቶ ቤተሰብን አካባቢንና ሀገርን መርቆ እኩይ ምግባራትንና ነገሮችን ረግሞ ክዋኔዉ ይጠናቀቃል። የሲቢታ ሄራ በክስታኔ ማኅበረሰብ ዘንድ ያለውን ኃይል የሚያሳየው ሌላው ጉዳይ የይቅርታና የምሕረት ጽንሰ ሐሳብ ነው። ሄራው ካለቀ በኋላ፣ የሚፈለግ ወንጀለኛ ወይም ደመኛ፤ ተበድሮ ወይም ዋስ ሆኖ የጠፋ፤ እንኳን ወደ ለቅሶው ቦታ ቢመጣ አትንኩት፤ ተብሎ ስለሚታወጅ ማንም ሊነካው አይችልም። ይህንን ህግ ተላልፎ የተገኘ በማህበረሰቡ ህግ የገንዘብ ቅጣት ይጣልበታል። ይህም

አጠቃላይ ህግ ግጭት የነበረባቸው ወገኖች በዚሁ መድረክ ላይ እርቅ እንዲያወርዱና ቂም ይዘው እንዳይቀጥሉ ዕድል በመስጠት ስነ-ልቦናዊ ፈውስን ያመጣል። የለቅሶ ሥርዓቱንም የሰላምና የደኅንነት መጠለያ ያደርገዋል።

## 3. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በክስታኔ ማኅበረሰብ የለቅሶ ሥነ ሥርዓት ውስጥ የሚፈጸመውን የሲቢታ ሜራ ክዋኔ ትዕምርታዊ ትርጓሜና ማኅበራዊ ፋይዳ የተመለከተ ነዉ። ሥርዓቱ እንዴት እንደሚከወን፣ በውስጡ የሚገኙት ትዕምርታዊ ድርጊቶች ምን ትርጉም እንዳላቸውና ለማኅበረሰቡ የሚሰጠውን ማኅበራዊ፣ ሥነ ልቦናዊና ፋይዳን ዓይነታዊ የጥናት ሥነ ዘዴን በመከተል በምልከታና በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች በክዋኔ ተኮር ንድፈ ሐሳብ ማዕቀፍ ውስጥ ገላጭ የይዘት ትንተና ዘዴዎችን በመጠቀም ተተንትነዋል።

የክስታኔ ማኅበረሰብ የለቅሶ ሥነ ሥርዓት ሀዘንን ከመግለጽ ባለፈ ጥልቅ ማኅበራዊ፣ ሥነ ልቦናዊና ባህላዊ ፋይዳ ያለው ነው።የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት የሆነው የሲቢታ ሜራ ክዋኔ፣ ማኅበረሰቡ የቤተሰብን ኃላፊነትና የወላጅ እንክብካቤን በአደባባይ ምስክርነት የሚያረጋግጥበት ልዩ ሥርዓት መሆኑን አሳይቷል። ይህ ሥርዓት ልጆች ወላጆቻቸውን በአግባቡ እንዲያገለግሉ የሚያስገድድ፣ ወላጆች ለልጆቻቸዉ ግዴታቸውን እንዲወጡ የሚያደርግ ያልተወጡትን ደግሞ በማኅበራዊ መገለል የሚቀጣ ማኅበራዊ ደንብ ነው። የሲቢታ ሜራ ሥርዓት ማኅበራዊ ፍትሕንና የሞራል ግዴታን ለማስፈጸም ያለው አቅም ከፍተኛ ነዉ።

ሥርዓቱ ሞትን እንደ መሸኛ ብቻ ሳይሆን በሕይወት ላሉት ግለሰቦች ከለላ መስጫ አድርጎ ይጠቀምበታል።ይህ የሲቢታ ሜራ በሟችና በሕያዋን መካከል ያለውን ማህበራዊ ውል የሚመረምርበት መንገድ እንደመሆኑ፣ በውስጡ የያዛቸው የምርቃትና የርግማን ትዕምርቶች በግለሰቦች የዕለት ተዕለት የሥነ-ምግባር አውድ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንዳላቸው ታይቷል። በተለይም ጎረቤቶች የሚሰጡት ምስክርነት ለሐዘንተኛው ቤተሰብ የሚሰጠው ስነ-ልቦናዊ ዋስትና እና የሕሊና እረፍት፣ ማህበረሰቡ በችግር ጊዜ ደራሽ መሆኑን በተግባር የሚያሳይ ነው። ይህ የባህል ተቋም በማህበረሰቡ ውስጥ ፍትህ እንዲሰፍን፣ ቂም እንዲወገድ እና ማህበራዊ ትስስር እንዲጠናከር በማድረግ ረገድ እንደ ዋነኛ መሣሪያ ሆኖ ሲያገለግል ቆይቷል።

የሲቢታ ሜራን የመሰሉ ጠቃሚ ባህላዊ እሴቶች ከዘመናዊው የሕግ ሥርዓት ጋር ተጣጥመው እንዲቀጥሉ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው። እነዚህ ሥርዓቶች በአገር በቀል እውቀትና በሰላም

ግንባታ ዙሪያ ለሚሰሩ እንደ ትልቅ ግብዓት ሊያገለግሉ ስለሚችሉ፣ በሰነድ ተመዝግበው ለቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፉ ሊደረግ ይገባል። በተለይም በትምህርት ተቋማት ውስጥ እንደ ማህበራዊ ትብብርና ሥነ-ምግባር ማስተማሪያነት ቢካተቱ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን የመረዳዳትና የመከባበር እሴት ይበልጥ ለማሳደግ ይረዳሉ። በተጨማሪም፣ የሀገር ሽማግሌዎች ያላቸውን ጥልቅ እውቀትና ተሞክሮ ከወጣቱ ትውልድ ጋር የሚያጋሩባቸው መድረኮች በስፋት ሊመቻቹ ይገባል። ይህንንም በማድረግ፣ የሲቢታ ሴራን መሰል የቆዩ ባህላዊ የፍትህና የሥነ-ምግባር መቆጣጠሪያ መንገዶች ይዘታቸውን ሳይለቁ ከወቅታዊው ማህበራዊ ለውጥ ጋር ተስማምተው እንዲሄዱና ለማህበረሰቡ ሁለንተናዊ ሰላምና መረጋጋት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ማድረግ ይቻላል።

የቃላት መፍቻ

ሴራ ህግ፣ ደንብ

በርቺ ግፍ

ኬር ሰላም

## የተጠቀሱ ምንጮች


ሐረገወይን ድፋባቸው። "የክስታንኛ የለቅሶ ግጥሞች" በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ 1974 ዓ.ም።

ተስፋ ገብረየስ። አይመለል። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1987 ዓ.ም።

ፈቃደ አዘዘ። የሥነ ቃል መምሪያ። አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት። 1991 ዓ.ም።

Kothari, C. R. Research Methodology: Methods & Techniques. 2nd ed. India, New International (P) Limited, Publishers. 2004. Koul, L. Methodology of Educational Research. New Dalhi: Vikas Publishing House PVT. Ltd. 2006.